# በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት

# የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ኤጀንሲ

## የ2010 ዓ.ም የ6 ወራት ሥራ አፈጻጸም ሪፖርት

ጥር/ 2010 ዓ.ም

## 1. መግቢያ

የሀገራችንን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማሳካት እስካሁን ያለው ልማዳዊ የመረጃ ሥርዓት ይበልጥ ዘመናዊ መሆን ስላለበት በተለይም ለፍትህ፣ ለአስተዳደርና ለስታቲስቲክስ ሥርዓቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ኩነቶች(Events) በተከሰቱበት ጊዜና ቦታ መዝግቦ ማደራጀትና ለሚፈልጓቸው አካላት በተፈለጉ ሰዓት ማቅረብ ስለሚገባ የዋና ዋና ኩነቶች መዝጋቢ አካል (Vital Events Registration Agency) ተቋቁሞ መዋቅሩን እስከ ቀበሌዎች በመዘርጋት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን አጠናቅቆ ወደ ሥራ የገባ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በክልላችንም ይኸው ጉዳይ ትኩረት ተሰጥቶት በደንብ ቁጥር 84/2006 የክልሉ ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ኤጀንሲ ለዜጐች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተጠቃሚነት፣ ለሕግ የበላይነት እና ተጠያቂነት የኩነት ምዝገባ በክልላችን ዋነኛ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ማየት ራዕዩ ሆኖ ተቋቁሟል፡፡

- የወሣኝ ኩነቶች ምዝገባን በጥራት መፈፀም የሚያስችል ተቋማዊ አቅም የመገንባት
- የተገልጋይና ባለድርሻ አካላትን ግንዛቤ በማሣደግ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የማስመዝገብ ባህል የማዳበር
- ዘመናዊ ቴክኖሎጂና አሰራርን በመጠቀም ደህንነቱ የተጠበቀ የመረጃ አያያዝና ቅብብሎሽ ስርዓት በመዘርጋት የተገልጋይ እና ባለድርሻ አካላትን የወሳኝ ኩነቶች መረጃ ፍላጎት የማርካት ተልዕኮም ተሰጥቶታል፡:

በዚህም መሰረት ኤጀንሲው የሌሎች ክልሎችን ተሞክሮ በመውሰድ በ2008 አጋማሽ ላይ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት እስኪካሄድ ድረስ ጊዜያዊ የሰው ኃይል ተሟልቶለት፣ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን አጠናቅቆ ሐምሌ 30/2009 ዓ.ም በይፋ ወደ ምዝገባ ሥራው ለመግባት ችሏል፡፡

በዚች አጭር ሰነድ ከሐምሌ 01/2009 እስከ ታህሳስ 30/2010 ዓ.ም ድረስ ያለውን የኤጀንሲውን ሥራ አፈጻጸም ፊዚካል ሪፖርት እንቃኛለን፡፡

## 2. ከሰው ሃይል አንጻር

### 2.1. <u>***ከክልል እስከ ወረዳ ያለዉ የሰዉ ሃይል መረጃ***</u>

| ተ.ቁ | የአስተዳደር እርከን | በመዋቅሩ የተፈቀደ የሰዉ ሃይል | የተሟላው የሰው ሃይል | % |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በክልል | **22** | **20** | **91** |
| 2 | በዞን | **3** | **3** | **100** |
| 3 | ከተማ አስ/ር | **3** | **2** | **67** |
| 4 | ልዩ ወረዳ | **3** | **2** | **67** |
| 5 | በወረዳ | **60** | **52** | **87** |
| | *ድምር* | **91** | **79** | **87** |

- ✓ በፎርም 15 ከተፈቀደው የሰው ኃይል በተጨማሪም የኤጀንሲውን ስራ ውጤታማ ለማድረግ 4 የኮንትራትና 2 የቀን ሰራተኞችን በመቅጠር እያሰራ ይገኛል፡፡
- ✓ በአሶሳ ከተማ አስተዳደር አዲስ የተዋቀሩ 6 ቀበሌዎች ላይ የሥራ ቸስኪያጅ ቅጥር ተፈጽሞ፣ ስልጠና በመስጠት ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

## *በመዋቅሩ ያለዉን የሰዉ ሃይል ለማሟላት እና በመዋቅሩ እንዲቆይ ለማድረግ ያጋጠሙን ችግሮች*

- በፎርም15 የተፈቀደ የሰው ኃይል በBPR ጥናት ሰነዱ ልክ ሳይሆን አጠቃላይ የክልሉን በጀት ባገናዘበ መልኩ ተቀንሶ መፈቀዱ
  - በፎርም15 ከተፈቀደው መዋቅር 2ቱ ዋና የሥራ ሂደቶች ምንም እንኳ በበጀት ቢደገፉም የሰው ኃይል አመዳደቡ በሹመት አግባብ በመሆኑ እስካሁን ሹመቱ ያልጸደቀ መሆኑ ያጋጠሙን ችግሮች ሲሆኑ፣ እንደመፍትሄ መፍትሄ ያሉት ስራዎች ባለው የሰው ኃይል እንዲሸፈኑ ተደርጓል፡፡

### 2.2. *በቀበሌ ደረጃ የሚገኝ የክብር መዝገብ ሹም መረጃ*

| የክብር መዝገብ ሹም | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የተሟላባቸዉ ቀበሌዎች ብዛት | | | | ያልተሟላባቸዉ ቀበሌዎች ብዛት | | | | ከ2009 ዓ/ም መጨረሻ ከነበረዉ አፈጻጸም ጋር የተሟላባቸዉ ቀበሌዎች ብዛት በንጽጽር | | የለቀቀባቸዉ ቀበሌዎች ብዛት | | | |
| በገጠር | በከተማ | ድምር | በ% | በገጠር | በከተማ | ድምር | በ% | 2009 | 2010 እስከ 6 ወር | በገጠር | በከተማ | ድምር | በ% |
| 448 | 38 | 486 | **100%** | **0** | **0** | **0** | **0** | 480 | 486(6ቱ አዲስ ቀበሌ) | **0** | **0** | **0** | **0** |

***ከክብር መዝገብ ሹሞች መልቀቅና ማሟላት ጋር ተያይዞ ያጋጠመ ችግር ፣ ችግሮችን ለመፍታት የተደረገ ጥረት፣ የተገኙ ዉጤቶች እና የቀጣይ አቅጣጫን በተመለከተ፡-***

*የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች በሥራ መዘርዝራቸው የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥራ እንዲካተት ተደርጎ የክብር መዝገብ ሹም ሥራን በሥራቸው ላይ ደርበው እንዲሰሩ መደረጉን ተከትሎ ከክብር መዝገብ ሹሞች ከሥራ መልቀቅ(Turn Over) ጋር ተያይዞ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት የተደረገ ጥረትን በተመለከተ የሥራ አስኪያጆችን የሥራ ጫና እና የጥቅማጥቅም ጥቄዎችን ለክልሉ መስ/ር ም/ቤት አቅርበን በክልሉ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ በኩል የጥቅማ ጥቅም መመሪያቸው ተሻሽሎ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በቀጣይ ይህ የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች የጥቅማ ጥቅም መመሪያ ለክልሉ መስ/ር ም/ቤት ቀርቦ ሲጸድቅ ችግሩ እንደሚቀረፍ ይጠበቃል፡፡*

## 3. *የመረጃ ቅበላ፣ አቅርቦትና አያያዝ ስራዎችን በተመለከተ*

### 3.1. ምዝገባ የጀመሩ ቀበሌዎች በተመለከተ፡-

| አጠቃላይ መረጃ | | | | የቀበሌ ብዛት | በገጠ | በከተማ | ድምር | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ዞኖች | 1 ከ/አስ/ርና 1 ልዩ ወረዳ | ***ወረዳዎች ብዛት*** | **ቀበሌዎች ብዛት** | ***ምዝገባ የጀመሩ ቀበሌዎች ብዛት*** | **450** | **32** | **482** | **99.2%** |
| **3** | **2** | 19 | **486** | ምዝገባ ያልጀመሩ ቀበሌ ብዛት | **0** | **4** | **4** | **0.8%** |
| | | | | ድምር | **450** | **36** | **486** | **100%** |

**ምዝገባ ያልጀመሩ ቀበሌዎች ምዝገባ እንዲጀምሩ እየተደረገ ያለ ጥረት እና የተገኘ ዉጤትን በተመለከተ**

በአሶሳ ከተማ አስተዳደር አዲስ ከተቋቋሙ ቀበሌዎች 4ቱ ሥራውን ለማስጀመር ተከታታይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ምዝገባውን ለመጀመር ዝግጅት ላይ መሆናቸውን አረጋግጠናል፡፡

### 3.2. *ከሃምሌ 1 /2009 - ታሕሳስ 30/2010 ዓ.ም የተመዘገበ ኩነት መረጃ*

| *ተ.ቁ* | *የኩነት አይነት* | *የ2010 እቅድ* | *የስድስት ወራት እቅድ /ከሐምሌ1-ታህሳስ 30/* | *የተመዘገበ ኩነት* | *በ%* | *ከተመዘገቡ ኩነት የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው* | *በ%* |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ልደት | 11558 | 5788 | 3104 | 54% | 3005 | 97% |
| 2 | ሞት | 1782 | 892 | 359 | 40% | 221 | 62% |
| 3 | ጋብቻ | 2880 | 1440 | 312 | 21% | 312 | 100% |
| 4 | ፍቺ | 232 | 116 | 16 | 13% | 8 | 50% |
| 5 | ጉዲፈቻ | 40 | 20 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| | ***ድምር*** | **16452** | **8236** | **3791** | 46% | **3546** | 94% |

***በተያዘው እቅድ መሰረት እንዳይፈጸም ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን በተመለከተ፡-***

- ከተያዘው እቅድ አንፃር ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ በእቅዱ መሰረት ለመፈፀም ከነበሩ ዋና ዋና ተግዳሮቶች የአንዳንድ አመራሮች ለሥራው ያላቸው ትኩረት ማነስ፣ የግንዛቤ ክፍተቱ ሙሉ በሙሉ አለመጥራት፣ የሥራ አስኪያጆቹ የሥራ ጫና እና የባሕል ተጽዕኖ(ፍቺን በባህላዊ መንገድ መፈጸም) ይገኙበታል፡፡
- ***እቅዱን በተሟላ ደረጃ ለማሳካት በየደረጃዉ ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት የሚገባቸው ጉዳዮችን በተመለከተ፡-*** በየደረጃው ያለው አመራር ሥራው የአገር ደህንነት ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን በፖለቲካዊ ትርጉም ተረድተው እንዲደግፍ ማድረግ ሲሆን የሥራ አስኪያጁን የሥራ ጫና በመቀነስ በግንዛቤ ፈጠራው ሥራ ላይም ከፍተኛ ትኩረት በማድረግ በታችኛው መዋቅር

በተቋሙ የራሱ ክብር መዝገብ ሹም ቢመደብ ወቅቱን የጠበቀና ጥራት ያለው መረጃ ለሚመለከተው አካል መላክ ይቻላል፡፡

- ***ተመዝግበው የምስክር ወረቀት የማይወስዱ ከሆነ የማይወስዱበት ምክንያትና የምስክር ወረቀት ክፍያ መጠን በምስክር ወረቀት አወሳሰድ ላይ ያሳደረውን ጫና በተመለከተ፡-*** በተለይ በሞት ኩነት ሰው ሞቶ ለምን እንከፍላለን በሚል እሳቤ እና ፍቺ 2ቱም ተፋቺዎች ለሰርተፊኬቱ እኩል ያለመቅረብና ለመውሰድ ፍላጎት ያለመኖር

### 3.3. የተመዘገበ ኩነት በከተማና በገጠር

| ተ.ቁ | የኩነት አይነት | የተመዘገቡ የኩነት ብዛት | | | | ድምር | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | **ከተማ** | % | **ገጠር** | % | | |
| **1** | **ልደት** | 840 | 27% | 2264 | 73% | 3104 | 54% |
| **2** | **ሞት** | 52 | 14% | 307 | 86% | 359 | 40% |
| **3** | **ጋብቻ** | 62 | 20% | 250 | 80% | 312 | 21% |
| **4** | **ፍች** | 6 | 38% | 10 | 62% | 16 | 13% |
| **5** | **ጉዲፈቻ** | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0% |
| | **ድምር** | **960** | 25% | 2831 | 75% | 3791 | 73% |

### 3.4. ***<u>የተመዘገቡ ኩነቶች ከጊዜ አኳያ</u>***

| *ተ.ቁ* | *የኩነት አይነት* | *የተመዘገቡ የኩነት ብዛት* | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ***ወቅታዊ ምዝገባ*** | | ***የዘገየ ምዝገባ*** | | ***ጊዜ ገደቡ ያለፈበት*** | | ***አጠቃላይ ድምር*** | |
| | | ***በቁጥር*** | ***በ%*** | ***በቁጥር*** | ***በ%*** | ***በቁጥር*** | ***በ%*** | ***በቁጥር*** | ***በ%*** |
| ***1*** | ***ልደት*** | 2855 | 92% | 49 | 2% | 200 | 6% | 3104 | 54% |
| ***2*** | ***ሞት*** | 359 | 100% | 0 | 0% | 0 | 0% | 359 | 40% |
| ***3*** | ***ጋብቻ*** | 300 | 96% | 0 | 0% | 12 | 4% | 312 | 21% |
| ***4*** | ***ፍች*** | 16 | 100% | 0 | 0% | 0 | 0% | 16 | 13% |
| ***5*** | ***ጉዲፈቻ*** | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0% |
| | ***ድምር*** | **3530** | 93% | **49** | 1% | **212** | 6% | 3791 | 73% |

***በወቅታዊ ምዝገባ አፈፃፀም ላይ ያጋጠሙ ችግሮች እና የተሰጠ መፍትሄን በተመለከተ፡-***

የግንዛቤ ማነስና የአካባቢ ባህል ተጽዕኖ  የወቅታዊ ምዝገባ ሽፋን እንዲያንስ ምክንያት ሆኗል፡፡

ወቅታዊ ምዘገባን ከማጠናከር አንጻር እየተሰራ ያለው ስራ እና የተገኘ ዉጤት፡- ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ፈጠራ፣ ከላይ እስከ ታች የምዝገባ አስተባባሪ ኮሚቴዎችን በማዋቀር ወደ ሥራ በማስገባትና ተከታታይነት ያለው የክትትልና ድጋፍ በማድረግ ወቅታዊ የኩነት ምዝገባ ሽፋን ከፍ ለማድረግ ተችሏል፡፡

## 3.5. ***መረጃ በማጣራት ሂደት የጥራት ችግር ስላለባቸዉ የተመለሱ ቅጾች መረጃ***

| ተ.ቁ | የኩነት አይነት | የተመዘገበ መረጃ | ከተመዘገቡት ቅጾች ከክልል የተመለሰ | በ% | በ2009 ዓ/ም ከፌዴራል እና ከክልል ከተመለሱ ቅጾች በማስተካከል ለፌዴራል የተላኩ | | ከ2010 ዓ/ም ከፌዴራል እና ከክልል ከተመለሱ ቅጾችን በማስተካከል ለፌዴራል የተላኩ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | ልደት | 3104 | 85 | | 182 | 83% | 25 | 29% |
| 2 | ሞት | 359 | 3 | | 40 | 68% | 2 | 67% |
| 3 | ጋብቻ | 312 | 0 | | 30 | 81% | 0 | 0% |
| 4 | ፍች | 16 | 0 | | 1 | 100% | 0 | 0% |
| 5 | ጉዲፈቻ | - | - | - | - | - | - | - |
| | ድምር | 3791 | 88 | | 253 | 80% | 27 | 31% |

***የሚመለሱ ቅጾችን መጠን ለመቀነስ በየደረጃዉ በሚገኙ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ መዋቅር የተደረገ ጥረት እና የተገኘ ዉጤትና የታችኛዉ መዋቅር የሚመለሱ ቅጾችን በማስተካከል ለክልል በመላክ ረገድ ያጋጠመ ችግር፣ የተሰጠ መፍትሄና የታየ ለዉጥን በተመለከተ፡-***

ተከታታይነት ያለው ድጋፍና ክትትል በማድረግ እንዲሁም ግንዛቤ በመፍጠር በድግግሞሽ ይታዩ የነበሩት የአመዘጋገብ ክፍተቶች የቀነሱበት ሁኔታ የታየ ሲሆን በበጀትና በተሽከርካሪ እንዲሁም የቀበሌዎች መልክዓምድራዊ አቀማመጥ ችግር የታችኛዉ መዋቅር የሚመለሱ ቅጾችን በማስተካከል ለክልል በመላክ ረገድ እንደ ተግዳሮት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 3.6. **ከጤና ተቋም የተላኩ ማሳወቂያ ወረቀቶች ብዛት**

| **ተ.ቁ** | **የኩነት አይነት** | **የተመዘገቡ የኩነት ብዛት** | **ከጤና ተቋም በተላከው ማሳወቂያ የተመዘገበ** | **በ%** |
|---|---|---|---|---|
| 1 | **ልደት** | 3104 | 700 | **22%** |
| 2 | **ሞት** | 359 | 46 | **13%** |
| | **ድምር** | **3463** | **746** | 22% |

***ከጤና ተቋማት የማሳወቂያ ወረቀቶች እንዲላኩ ለማድረግ ከጤና መዋቅሩ ጋር በትስስር ለመስራት የተደረጉ ጥረቶች እና የተገኙ ዉጤቶች፣ የክልሉ ጤና ቢሮ የማሳወቂያ ወረቀት አሳትሞ ለመንግስት እና ለግል ጤና ተቋማት ከማሰራጨት አንጻር ያለበት ደረጃና በጤና ተቋማት የተሰጡ የማሳወቂያ ወረቀት ወደ ምዝገባ ጣቢያ ይዘው መጥተው መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ተግባራዊ የተደረገ አሰራርን በተመለከተ፡-***

ከጤና ተቋማት ጋር የመግባቢያ ሰነድ የመፈራረም ስራ ከክልል እስከ ወረዳ ባሉት መዋቅሮቻችን ተከናውኗል፡፡ በዚሁም መሰረት የግንዛቤ መፍጠር ሥራውን በጋራ እስከ ታችኛው መዋቅር ጤና ኤክስቴንሽ ባለሙያዎች ድረስ በጋራ በማከናወን የማሳወቂያ ወረቀቶቹ ለሁሉም የመንግስትና የግል ጤና ተቋማት፣ ለወረዳ መስተዳድሮችና ለወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች በማሰራጨት የማሳወቅ ሥራውን እንዲሰሩና አስመዝጋቢዎች የማሳወቂያ ወረቀቱን ይዘው ወደ ምዝገባ ቦታ ሄደው እንዲያስመዘግቡ ተደርጓል፡፡

***ከጤና ተቋማት የማሳወቂያ ወረቀቶች እንዲላኩ በማድረግ ረገድ ያጋጠሙ ችግሮች እና የተሰጡ መፍትሄዎች፡-*** ካጋጠሙን ችግሮች ዋነኛው የግንዛቤ ክፍተት (በተለይም በግል ጤና ተቋማት) ሲሆን ሌላውም በቅዳሜና እሁድ የትርፍ ሰዓት ሥራ ጊዜ ለሚከሰት ኩነት የማሳወቂያ ወረቀቱን ወጪ በማድረግ ዙሪያ ነበር፡፡ **እንደመፍትሄ** በተገኙት ማንኛቸውም መድረኮች ሁሉ በቅንጅት ግንዛቤ የመፍጠሩን ሥራ ተሰርቷል እየተሰራም ይገኛል፡፡

## 3.7. ***<u>መረጃ ቅበላና ማደራጀትን በተመለከተ</u>***

| ተ.ቁ | የኩነት አይነት | ቅበላ የተደረገ እና የተደራጀ የኩነት ብዛት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቅበላ | | | የተደራጀ | | |
| | | እቅድ | ክንዉን | በ% | እቅድ | ክንዉን | በ% |
| 1 | ልደት | 5788 | 3189 | 55 | 5788 | 3104 | 97 |
| 2 | ሞት | 892 | 362 | 41 | 892 | 359 | 99 |
| 3 | ጋብቻ | 1440 | 312 | 22 | 1440 | 312 | 100 |
| 4 | ፍች | 116 | 16 | 14 | 116 | 16 | 100 |
| 5 | ጉዲፈቻ | 20 | 0 | 0 | 20 | 0 | - |
| | ድምር | **8236** | **3879** | 47 | **8236** | **3791** | 98 |

***የመረጃ ቅበላ እና ማደራጀት ስራዉን ዉጤታማ ለማድረግ የተከናወኑ ስራዎች እና የተገኙ ዉጤቶች እንዲሁም ሥራው ላይ ያጋጠሙ ችግሮች እና የተሰጡ መፍትሄዎችን በተመለከተ፡-***

የመረጃ ቅበላ እና ማደራጀት ስራዉን ዉጤታማ ለማድረግ ከተከናወኑ ስራዎች

- ኤጀንሲው 17 ክፍሎች ያሉትና G+1 ህንጻ ያለው የሆነ ራሱን የቻለ ግቢ ተከራርቶ የተሸለ ምቹ አካባቢ አደራጅቶ እየሰራ ሲሆን ለዘለቄታው በ3 ዓመታት ተገንብቶ የሚያልቅ የኤጀንሲው የራሱ ቢሮ እንዲኖረው በክልሉ መንግስት 2000 ካሬ ሜትር ቦታ ምሪት ተፈቅዶ በአሁኑ ሰዓት የይዞታ ማረጋገጫ ሳይት ፕላን የተረከብን ሲሆን ግቢውን በአጥር ለማስከበር፣ የህንጻ ግንባታውን ዲዛይን ለማዘጋጅትና ለግንባታው የሚሆን ገቢ ለማሰባሰብ እንቅስቃሴ ላይ እንገኛለን፡፡
- ኮምፒዩተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ ጠረጴዛዎችና ፋይል ካቢኔቶች ተገዝተው ለአብዛኞች ወረዳዎች መሰራጨታቸው፣
- የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ተጠንቶ የመረጃ ቴክኖሎጂ የሥራ መደብ መከፈቱ፣ በበጀት መደገፉና በሰው ኃይል መሸፈኑ፣ የሚጠቀሱ ሲሆኑ የተተነተነ መረጃ በማቅረብ ላይ ግን

ውሱንነት የሚታዩ ሲሆን በቀጣይ ባለሙያው የክህሎት ስልጠና ወስዶ ወደ ሥራ ሲገባ ችግሮቹ እንደሚቀንሱ ይጠበቃል፡፡

### 3.8. **የስልጠናና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በተመለከተ**

#### 3.8.1 ስልጠና

| *ተ.ቁ* | *በክልል ደረጃ የተሰጠ ስልጠና ርእስ* | *በስልጠናዉየተሳፉ አካላት* | *በስልጠናዉ የተሳተፉ አካላት ብዛት* | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | *እቅድ* | *አፈጻጸም* | | | |
| | | | | *ወንድ* | *ሴት* | *ድምር* | *በ%* |
| *1* | *በወሳኝ ኩነት ምዝገባ ጽንሰ ሀሳብ፣ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ፣ ክፍተቶችና ቅንጅታዊ አሰራር ዙሪያ፣ እንዲሁም በቢ ኤስ ሲ እና መልካም አስተዳደር ዙሪያ* | *ለክልል፣ዞንና ወረዳ የወሳኝ ኩነት ባለሙያዎች፤* | *87* | *45* | *19* | *64* | *74%* |

በቀጣይ በተሸሻሉ አዋጅና መመሪያ ላይ ለክብር መዝገብ ሹሞች ስልጠና ለመስጠት ቅድመ ዝግጅት ላይ እንገናለን፡፡

- ***በተሰጠው ስልጠና የመጣ ለዉጥን በተመለከተ፡-*** የአመዘጋገብ ክፍተቶች ተሸሽለዋል፣ ቅንጅታዊ አሰራር ተሻሽሏል፡፡
- ***ከስልጠና ጋር ተያይዞ ያጋጠሙ ችግሮች እና የተሰጠ መፍትሄ፡-*** የበጀት ውስንነት፣ የተሽከርካሪ፣ የጋራ ግዥ ሂደት መጓተት/በተለይ በስቴሽነሪ ግዢዎች/ የገጠሙን ሲሆን ባለው ውስን በጀትና ተሽከርካሪ ስራዎቹ ተከናውነዋል፡፡

#### ***3.8.2 ግንዛቤ ፈጠራ***

| *የግንዛቤ ፈጠራዉ ያተኮረበት ጉዳይ* | *ግንዛቤ የተፈጠረላቸዉ አካላት* | *በግንዛቤ ፈጠራዉ የተሳተፈ የህብረተሰብ ክፍል ብዛት* | | | | *አፈጻጸም በ%* |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | *እቅድ* | *አፈጻጸም* | | | |
| | | | *ወንድ* | *ሴት* | *ድምር* | |
| *በወሳኝ ኩነት ምዝገባ ጽንሰ ሀሳብ፣ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ፣ በልደትና በሞት ማሳወቂያ አሞላል፣ እንዲሁም በታዩ አመዘጋገብ ክፍተቶችና ቅንጅታዊ አሰራር ዙሪያ* | *ለዞንና ወረዳ አመራሮች፤* | | *85* | *17* | *102* | |
| | *ለክልል፣ዞንና ወረዳ የወሳኝ ኩነት ባለሙያች፤* | | *68* | *19* | *87* | |
| | *ለጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች፤* | | *0* | *988* | *988* | |
| | *ለዳንጉር፣ ካማሽና ባምባሲ ወረዳ ርዕሰ መምህራኖች፤* | | *87* | *10* | *97* | |
| | *በሐደረጀጀት ዘርፍ ኃላፊዎች* | | *77* | *5* | *82* | |
| | *የቀበሌ ዋና ስራአስኪያጆች* | | *78* | *0* | *78* | |
| | *የቀበሌ ሥራ ስአኪያጆች* | | *55* | *25* | *80* | |
| | *የሴቶች ተወካዮች* | | *0* | *77* | *77* | |
| | *ሌሎች የኅ/ሰብ ክፍሎች* | | *54879* | *35312* | *90191* | |
| | ***ድምር*** | **240,600** | **55329** | **36453** | **91782** | ***38%*** |

**በኮሙኒኬሽን ሥራ የተፈጠረ ግንዛቤን በተመለከተ**

- ✓ በአሶሳ ኤፍ ኤም ሬድዮ በየሳምንቱ 2 ቀናት አርብና ረቡዕ የ40 ደቂቃ ፕሮግራም የአየር ሰዓትን በመከራየት፣
- ✓ ስልጠናዎች ሲካሄዱ ፕሮግራሞችን በማሰራት በበዓላት ቀን የክብር እስፖንሰር በማድረግ በቤጉ ቲቪ መልዕክቶች እንዲተላለፉ በማድረግ፣
- ✓ በቤጉህዴፓ ልሳን ጋዜጣ በየወሩ 1 ገጽ በመከራየት፣
- ✓ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ከ49000 ብር በላይ ውል ገብቶ በመክፈል በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚታተመው ፎን ቡክ ላይ የኤጀንሲውን ራዕይ ተልዕኮና ዕሴቶች የማስዋወቅ ሥራ በመስራት፣
- ✓ 1500 ብሮሸሮችን በማሰራጨት
- ✓ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥራ የተጀመረበትን 1ኛ ዓመት በዓል በባህል ቡድን አባላት በማጀብ በደማቅ ሁኔታ ለማክበር የተለያዩ ባነሮችን በማዘጋጀት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽንሰ ሀሳብ፣ ጠቀሜታና አስፈላጊነት ዙሪያ ኅ/ሰቡ ግንዛቤ እንዲያገኝ በማድረግ የኤንሲውን የሥራ እንቅስቃሴ የማስተዋወቅ ሥራ ተሰርቷል፡፡

◈ ***በተፈጠረዉ ግንዛቤ የመጣ ለዉጥን በተመለከተ፡-*** የወረዳዎች በጀት አመዳደብ ተሻሽሏል፣ ኅ/ሰቡ ስለ ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ያለው አመለካከት ተሻሽሏል፣ የኅ/ሰቡ ኩነትን የማስመዝገብ ተነሳሽነት ጨምሮ ኩነት የማስመዝገብ ባህሉ ዳብሯል፡፡

◈ ***ከግንዛቤ ፈጠራዉ ጋር ተያይዞ ያጋጠሙ ችግሮች እና የተሰጠ መፍትሄ፡-***

የበጀት ውስንነት፣ የተሽከርካሪ፣ የጋራ ግዥ ሂደት መጓተት/በተለይ በስቴሽነሪ ግዢዎች፣ በዕቅዱ መሰረት የተፈለገውን የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ተሳታፊዎችን ለማግኘት የአመራሩ በደራሽ ስራዎች መጠመድ እንደተግዳሮት የገጠሙን ሲሆን ባለው ውስን በጀትና ተሽከርካሪ ስራዎቹ ተከናውነዋል፡፡

### *3.8.3. <u>የምዝገባ ግብአቶችን በማሟላት ረገድ</u>*

- ✓ ***ለ2010 በጀት አመት ምዝገባዉን ለማከናወን ወሳኝ የሆኑ የክብር መዝገብ እና የምስክር ወረቀት በማሳተም ረገድ፡-*** በ2010 ዓ.ም በክልል ደረጃ ለሕትመት ብር 1,000,000 የተመደበ ሲሆን በዚህ 6 ወራት ውስጥ ህትመትን በተመለከተ በዕቅድ የተያዘና የተሰራ ስራ ባይኖርም በቀጣይ 6 ወራት ውስጥ የሚያስፈልገውን የምስክር ወረቀትና የክብር መዝገብ ብዛት በማጥናት ከአሳታሚ ድርጅቶች ጋር ውል በመግባት የሚታተም ይሆናል፡፡

✓ ***የክብር መዝገብ እና የምስክር ወረቀት በማሳተም ረገድ የጋጠሙ ችግች እና የተሰጡ መፍትሄዎችን በተመለከተ፡-***

በበጀት ዓመቱ ለህትመት ብር 1,000,000 በዕቅድ በያዝነው መሰረት በዚህ ግማሽ ዓመት የህትመት ውጤቶች ግብዓት ፍላጎት ባለመቅረቡ እስካሁን ያላሳተምንና በቀጣይ ፍላጎትን መሰረት በማድረግ የምናሳትም ሲሆን ከዚህ ህትመት ጋር ተያይዞ የገጠመን ችግር የለም፡፡